የሠ/መ/ቁ/ 43934

ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ፌ/ዐ/ህግ አቶ ፈቃዱ ፀጋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ቴዎድሮስ ካሣሁን ጠበቆች 1. አቶ ሚሊዮን አሰፋና
2. አቶ አመነ በድሉ } ቀረቡ

ተጠሪም ከማረ/ቤት ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የመሠረተው የወንጀል ክስ በሁለት ምድብ (count) የተከፈለ ሲሆን 1ኛው ክስ ተጠሪ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/አንቀጽ 543(3) እና የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 279/1956 አንቀጽ 5(4) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተሽከርካሪን ለማሽከርከር የሚያስችል መንጃ ፍቃድ ሣይኖራቸው ጥቅምት 23 ቀን 1999 ዓ.ም ከሌሊቱ 7፡10 ሲሆን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-59869 አ.አ የሆነ ቢ.ኤም ደብሊው አውቶሞቢል እያሽከረከሩ ሲጓዙ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 ልዩ ቦታው ፊት በር ከተባለ አካባቢ ሲደርሡ መንገዱን ከቀኝ ወደ ግራ በማቋረጥ ላይ የነበረውን ሟች ደጉ ይበልጣል የተባለውን ቅድሚያ በመከልከል ገጭተው በመግደላቸው በቸልተኝነት ሠው መግደል

ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ሲሆን፣ 2ኛው ክስ ደግሞ ተጠሪ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/አንቀጽ 575(2/ሀ)ን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተመለከተው ጊዜና ቦታ የሰሌዳ ቁጥር 2-59869 አ.አ የሆነው ቢ.ኤም ደብሊው አውቶሞቢል እያሽከረከሩ ሲጓዙ ሟች ደጉ ይበልጣል ይባል የነበረውን ከገጩ በኋላ ተገጭው ህይወቱ በከባድ አደጋ ላይ መሆኑን እያወቁ እርዳታ ሣያደርጉለት ጥለው ስለሸሹ በአደጋ ላይ  የሚገኝ ሠው አለመርዳት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪም የዐ/ህግ ክስ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ሲጠየቁ በክሡ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ዐ/ህግ በበኩሉ እንደ ክስ አመሠራረቱ የሚያስረዱ የሠውና የሠነድ ማስረጃዎች ያሉት መሆኑን በገለፀው መሠረት ማስረጃዎቹ ተሠምተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የተከሠሡባቸውን የወንጀል ድርጊቶች መፈፀማቸውን ዐ/ህግ የአስረዳባቸው መሆኑ ተገልፆ የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብታቸው ተጠብቆላቸው የሠውና የሠነድ ማስረጃዎችን አቅርበው እያንዳንዱ የመከላከያ ማስረጃ ሊያረጋግጥላቸው የሚገባውን ጭብጥ በማስያዝ ማስረጃዎቻቸውን አሠምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ለትክክለኛ ፍትህ አሠጣጥ ሲል ማጣሪያ ይሆናሉ ያላቸውን ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር ተገቢነት አላቸው ያላቸውን ጭብጦችን በመመስረት የተጠሪን መከላከያ ማስረጃዎችን በመመዘን የዐ/ህግን ማስረጃዎች ሊያስተባብሉ የሚችሉ አይደሉም ሲል ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በዐ/ህግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡት በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ ናቸው ሲል ወስኗል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት ጠይቆ ዐ/ህግ ተጠሪ የፈፀሟቸው ወንጀሎች ተደራራቢ መሆናቸውን በአደጋ ላይ የነበረውን ሟች ህይወቱ አደጋ ላይ መሆኑን

እያወቁ እርዳታ ማድረግ ሲገባቸው ይህንኑ ተጠሪ ያለማድረጋቸውንና ወንጀሉን የፈፀሙትም የመንጀ ፍቃድ ሣይኖራቸው በማሽከርከር መሆኑን ጠቅሰው እነዚህ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ ቅጣት እንዲወሰን አስተያየት ሲሰጡ የተጠሪ ጠበቆች በበኩላቸው ተጠሪ ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም ብለው የሚከራከሩ መሆናቸውን በመግለፅ የሚያቀርቡት የቅጣት አስተያየት የሌላቸው መሆኑን አስመዝግበዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በቅጣት አወሣሰኑ በህጉ ላይ የተመለከቱትን መርሆዎችን መከተሉን ገልፆ በ1ኛው ክስ በ5/አምስት/ ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 13,000.00/አስራ ሦስት ሺህ/፣ በ2ኛው ክስ በህጉ ላይ የተመለከተውን ቀላል የእስራት ቅጣት በወንጀል ህጉ 184(1/ለ) መሠረት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት በመቁጠር የ1/አንድ/ ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ በድምሩ በ6 (ስድስት) ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 18,000.00/አስራ ስምንት ሺህ ብር/ መቀጮ ተጠሪ እንዲቀጡ ወስናል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሠሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶ ቅጣቱን በተመለከተ ግን ለአደጋው መድረስ የሟች አስተዋጽኦ ከፍተኛ የነበረ ስለመሆኑ በዐ/ህግ ማስረጃዎች መረጋገጡንና ይህም ሁኔታ በወ/ህጉ አንቀጽ 86 መሠረት በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚገባው መሆኑን፣ የጥፋቱን ተደራራቢነትም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጉዳዩን ከህጉ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ማመዛዘኑን ጠቅሶ ቅጣቱን በወ/ህጉ አንቀጽ 179(ሐ) መሠረት በማቅለል የስር ፍ/ቤት በተጠሪው ላይ ያስተላለፈውን የቅጣት መጠን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ-2) መሠረት በማሻሻል ተጠሪ በጉዳዩ ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ ታስረው የቆዩበት ጊዜ በሚታሠብ በ2/ሁለት/ ዓመት ፅኑ

እስራትና በብር 11,000.00 /አስራ አንድ ሺህ ብር/ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት ውሣኔ ነው፡፡

አመልካች በቁጥር 5-6922/01663/01 በቀን 24-06-2001 ዓ.ም 4/አራት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ወንጀል ይግባኝ ሠሚ ችሎት በቅጣት አወሣሰን ረገድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ይግባኙ የቀረበው የጥፋተኝነት ውሣኔ በመቃወም ብቻ ሁኖ ቅጣቱን በተመለከተ በይግባኝ ጊዜ ቀርቶ በስር ፍ/ቤት በተደረገ ክርክር ወቅትም ተጠሪ አለመከራከራቸውን፣ የወንጀል ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤት ስልጣን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195 ስር መመልከቱንና የቅጣት ውሣኔው ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ ውጪ መሆኑን ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተሣሣተ ፍሬ ነገር ላይ በመመስረት የተሣሣተ የህግ ትርጉም መስጠቱን፣ ፍ/ቤቱ በቀለለ ቅጣት ላይ ማቅለያ አቅርቦ ቅጣቱን ከመነሻ ዝቅ አድርጐ መወሠኑ የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን ተደራራቢ ወንጀሎች መፈፀማቸው ተረጋግጦና የጥፋተኝነት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ በፀናበት ሁኔታ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በቀረቡበት ሁኔታ የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሠጠበት አንቀጽ መነሻ ቅጣት ዝቅ ተደርጐ ቅጣት መተላለፉ ህጋዊ አካሄድ አለመሆኑን፣ ይህም የፍትህ ስርዓቱን ተገማችነት /Predictability/ እንዳይኖረው የሚያደርግ ስለመሆኑና ይግባኝ ሠሚው ችሎት በሌሎች በተመሣሣይ ክስ ጥፋተኛ ለተባሉት ይግባኝ ባዮች ከመነሻው ሣይወርድ ቅጣት ሲያተላለፍ ቆይቶ በተጠሪ ጉዳይ ቅጣቱን ዝቅ ማድረጉ የፍትህ ስርዓቱን ተገማች እንዳይሆን የሚያደርግና የዜጐችን እምነት የሚሸረሽር መሆኑን ዘርዝረው ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላለበት ታርሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው የቅጣት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪ በተደራራቢ

ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉበት ውሣኔ በይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ፀንቶ እያለ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ከመነሻው ዝቅ አድርጐ መወሠኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በዚህ ሠበር ችሎት ሊመረመር የሚገባው መሆኑ ታምኖበት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሠኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡ ዐ/ህግ የሠበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ከመከራከራቸውም በተጨማሪ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሠሚ ችሎት የገንዘብ መቀጮውን የቀነሠበት አግባብም በህጋዊ ምክንያት አለመደገፉን ዘርዝረው በሠበር አቤቱታ ላይ የጠየቁት ዳኝነት እንዲሠጥ ይህ ካልሆነም ይህ ችሎት ተገቢውን የቅጣት መጠን እንዲያስተላልፍ ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ ጠበቆች በበኩላቸው የዐ/ህግ ቅሬታ በወንጀል ህጉ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ መሆኑን የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሰን ለጥፋቶቹ ቅጣቱን ለያይቶ ካለማስቀመጥ በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ይልቁንም ተጠሪ እንዲቀጡበት የተላለፈውን የቅጣት መጠንን ያህል የሚያስቀጣ ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ጠቅሰው ይህ ችሎት ቅጣቱን ለመጨመር፣ ለመቀነስ ወይም ለማፅናት ስልጣን ያለው በመሆኑ ተጠሪ የታሠሩበትን ጊዜ በቂ በማድረግ ከእስር እንዲፈቱ እንዲወሰን ወይም የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲያፀና ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካች የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት ከሚልባቸው ምክንያቶች አንዱ ተጠሪ በይግባኝ ማመልከቻቸው ይግባኝ የጠየቁት በጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ የስር ፍ/ቤት ህዳር 22 ቀን 2001 ዓ.ም ባስተላለፈው ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ ይህንኑ መሠረት አድርገን ተጠሪ ለይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ታኅሣስ 08 ቀን 2001 ዓ.ም የፃፉትን የይግባኝ ማመልከቻ የወ/ይ/መ/ቁ 41954 የሆነውን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም የተጠሪ የይግባኝ ማመልከቻ የስር ፍ/ቤት በሠጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ ላይ የቀረበ ስለመሆኑ በገፅ አንድ በግልፅ ያሠፈረ ከመሆኑም በላይ በማመልከቻው ገፅ 12 ላይ የስር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪ እንዲከላከሉ በሠጠው ብይን ህዳር 22 ቀን 2001 ዓ.ም በሠጠው የጥፋተኝነት ውሣኔና ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም በሠጠው የቅጣት ውሣኔ የቀረበ ስለመሆኑ በሚያሣይ መልኩ ተጠቅሶ እነዚህ ብይኖችና ውሣኔዎች እንዲሻሩላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ስለሚያሣይ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የተጠሪን የይግባኝ ማመልከቻ ሙሉ ይዘትና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2) (ለ-2) ስር የተመለከተውን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት እንዲሁም የይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤትን ስልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

የአመልካች መሠረታዊ ክርክር የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሰን በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮችና የቅጣት አወሣሠኑን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ እኛም ይህንኑ ቅሬታ ከህጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ

ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችን የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስንና የቅጣት አወሣሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ (Manual) እንደሚወጣ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው አቢይ ነጥብ ቅጣቶች መወሠን ያለባቸው የህጉን መንፈስ በመከተል ዓላማዎችንና ግቦቹንም ተፈፃሚ በማድረግ ሀሣብ መሆኑን ነው፡፡ የህጉን መንፈስ ከመተግበር አኳያ ወንጀለኛውን ማዕከል የማድረግ ፅንሰ ሀሣብ አጽንኦት የተሠጠው ጉዳይ ነው፡፡ ዳኞች በፅንሰ ሀሣቡ መሠረት የተሠጣቸውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን (Discretion) በስራ ላይ ሲያውሉ ሠብአዊ ክብርን ከማስጠበቅ ዓላማ ጋር መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ህግ አውጪው በአንቀጽ 87 እና 1 ስር የተመለከቱትን መሠረት በማድረግ ዳኞች የቅጣት ውሣኔ በምን መንገድ መወሠን እንደሚገባቸው በአንቀጽ 88 ስር አስቀምጧል፡፡ በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ስንመለከትም ዳኞች ከተሠጣቸው የቅጣት ክልል ሣይወጡ የአጥፊውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት እንዲወስኑ ህጉ ስልጣን የሠጣቸው መሆኑ ነው፡፡ ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሣሠናቸው መሠረት የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual quilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ የዘትና አቀራረፅ ያስረዳል፡፡ ይህም በቅጣት አወሣሠን ወቅት ዳኞች ሠፊ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡ አንቀጽ 88(2) በመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን መሠረት በማድረግ ዳኞች ቅጣት እንዲወስኑ ማድረጉና ይህንን ሲወስኑም በድንጋጌው የተመለከቱትን የወንጀሉን አፈፃፀም የአንጥፊውን ያለፈ የህይወት ታሪኩንና የኑሮ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በማመዛዘን ለወንጀሉና ለወንጀለኛው የሚገባውን የቅጣት መጠን እንዲወስኑ መደንገጉ የቅጣት ውሣኔዎችንና እርምጃዎችን እየተራራቁ እንዳይወሠኑ የማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ከመታሠቡም በተጨማሪ ችግሩ የሚቀረፍበትና የሚቀነስበትን ሥርዓትም ህጉ ዘርግቷል፡፡ ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ በህጉ አንቀጽ 88(2) ለአጥፊው ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት ከወሠኑ በኋላ

በህጉ የተመለከቱትን የማቅለያና የማክበጃ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ ህጉ ያሣያል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ በአንቀጽ 82(1) ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (ሠ) ድረስ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ካስቀመጠ በኋላ በአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከቱት የማቅለያ ሁኔታዎች በህጉ ልዩ ክፍል ተካተው ሲገኙ በድጋሚ በማቅለያነት ዳኞች እንዳይጠቀሙ ያሣስባል፡፡ የህጉ አንቀጽ 84 ደግሞ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን የዘረዘረ ሲሆን ዳኞች የህጉን አንቀጽ 183 ባገናዘበ መልኩ ቅጣት የሚያከብዱባቸውን ሁኔታዎች ያሣያል፡፡ ዳኞች ቅጣትን የሚቀንሱትም ሆነ የሚያከብዱት ተገቢ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአንቀጽ 179 እና 183 ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ አንቀጽ 179 የቅነሣውን ገደብ የሚያሣይ ሲሆን ከዚህ መደበኛ ቅነሣ በተጨማሪ ልዩ ቅነሣ ለማድረግ እንደሚቻልም ህጉ በአንቀጽ 180 ስር አስቀምጧል፡፡ በህጉ አንቀጽ 86 ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ከህጉ አንቀጽ 179፣ 182 እና ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥማቸው ዳኞች ምክንያታቸውን በመግለፅ ቅጣቶችን ለመቀነስ ወይም ለማክበድ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ተደራራቢ ጥፋቶች በአንድ ወንጀለኛ ተፈፅመው ሲገኙም ቅጣትን ማክበድ እንደሚገባ ህጉ በአንቀጽ 184(1/ለ) ስር ደንግጓል፡፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ ከሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡና ነፃነትን የሚያሣጡ ቅጣቶችን የሚያስከትሉ ተደራራቢ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ እንደሚደመር፣ ሆኖም ለቅጣቱ ዓይነት በህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ የማይችል ስለመሆኑና በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ አፈፃፀሙ የሁለት ዓመት ቀላል እስራት ቅጣት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የሚቆጠር መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ይህ ድንጋጌም ቢሆን

ህጉ በመርህ ደረጃ በአንቀጽ 88(2) መሠረት ለዳኞች የሠጠውን አመዛዝኖ የመወሠን ስልጣን የሚገድብ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ስለቅጣት አወሣሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ዓቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሠድ ረገድ ዳኞች አመዛዝነው የመወሠን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ስልጣን አንዳንድ ህጋዊ ገደቦች የተደረጉበት ቢሆንም ቅጣቶች እጅግ እየተራራቁ እንዲወሰኑ ሊያደርግ እንደሚችል ግልፅ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አሠራር ጨርሶ ይቀራል ተብሎ ባይታሠብም የዳኞች ሥልጣን እንዲጠብ ግን ማድረግ ይችላል፡፡ ህግ አውጪው የዳኞችን ስልጣን እንዲጠብ ሊያደርግ ይችላል ብሎ የዘረጋው የቅጣት አወሣሰን መመሪያን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ህጉ ከወጣበት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሰን መመሪያ አላወጣም፡፡

እንግዲህ ህጉ ለዳኞች የሠጠውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን ይኸው ስልጣናቸው እንዲጠብ የዘረጋውን ሥርዓትና የስርዓቱን ተግባራዊ አለመሆን ከላይ ተመልክተናል፡፡ ዐ/ህግ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከተው ከመነሻው ይግባኝ ሠሚው ችሎት በተሣሣተ ፍሬ ነገር ህጉን መተርጐሙን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አለመኖሩን እና የቅጣት ማቅለያው አለ ቢባል እንኳ የወንጀሉ ማቋቋሚያ የሆነው ነገር ስለመሆኑ ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተሣሣተ ፍሬ ነገር ይዟል መባሉ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤትን ዋና መዝገብ አስቀርቦ ሲመለከት ለአደጋው መድረስ የሟች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበር በማለት ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የመዘገበው ፍሬ ነገር የሟቹ በአስፓልት ወድቆ የነበረ መሆኑ በህግ ምስክሮች የተነገረ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ፍ/ቤቱ ይዞ በቅጣት ማቅለያነት መወሰዱም የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 86 ስር የሠጠውን ስልጣን መጠቀሙን ያሣያል ከሚባል

በስተቀር የሚነቀፍበት መሠረታዊ የሆነ የህግ ነጥብ የለም፡፡ ይግባኝ ሠሚው ችሎት ለወንጀሉ ማቋቋሚያ የሆነ ምክንያት ቅጣቱን ለማቅለል ስለመጠቀሙም የውሣኔው አፃፃፉና መንፈሱ የሚያሣይ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ዐ/ህግ ያቀረቡት ቅሬታ ህጋዊ መሠረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት በዐ/ህግ ማስረጃዎች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ለቅጣት ማቅለያነት የተጠቀመው በ1ኛው ክስ ለተፈፀመው ጥፋት ስለመሆኑ ለውሣኔው ዋቢ ያደረገው ድንጋጌ እና የውሣኔው መንፈስ ያሣያል፡፡ በእርግጥ ይግባኝ ሠሚው ችሎት ጥፋቱ ተደራራቢ መሆኑን እየገለፀ የቅጣት ውሣኔውን ነጣጥሎ አለመወሠኑ በህጉ አንቀጽ 184(1/ለ) ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በአንቀጽ 543(3) ስር የተመለከተውን መነሻ ቅጣት ተገቢ መስሎ ሲታየው በህጉ አንቀጽ 108(1) የተመለከተውን የፅኑ እስራት ቅጣት መነሻ ሣይወርድ ማቅለል የሚችል ስለመሆኑ የአንቀጽ 179(ሐ) ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ከዚህ በህጉ ለዳኞች ከተሠጠው ስልጣን አኳያ ሲታይ ይግባኝ ሠሚው ችሎት የደረሠበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንደሚታወቀው የዚህ የሰበር ችሎት አላማ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ማረም ነው፡፡ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዉ የሆነ የህግ ስህተት ሊሆን የሚችለው ህጉ ለዳኞች የሚሠጠውን አመዛዝኖ የመወሠን ስልጣንን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሣሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሠረታዊ መርሆዎች ጥሰው ሲገኙ መሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የቅጣት አነሠ በዛ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት ለማለት የሚያስደፍር ነው፡፡ በመሆኑም ጥፋቶቹ ተደራራቢ ሁነው እያለ ከመነሻው ዝቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚለው የዐ/ህጉ ቅሬታ ህጋዊ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው ዐ/ህግ አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ የተገማችነት /Predictability/ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ክርክራቸው ዐ/ህግ መሠረት ያደረጉት ምክንያት ተጠሪ ጥፋተኛ በተባሉበት ተመሳሳይ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባሉትን ይግባኝ ባዮች ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ቅጣቱን ከመነሻው አለመውረዱን ነው፡፡ በእርግጥ የፍትህ ስርዓቱ ተገማች እንዲሆን ይጠበቃል ይሁን እንጂ በቅጣት አወሣሰን ረገድ ለዳኞች የሚሠጠው ቅጣት ከወንጀለኛው አንፃር የመወሰን ስልጣን በህጉ ጥበቃ በተደረገበት ሁኔታና ይህንኑ ሥልጣን ለማጥበብ ይረዳል ተብሎ የሚታሰበው የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ባልወጣበት ሁኔታ ተመሣሣይ አንቀጽ ጥፋተኛ ለተባሉ ሠዎች የቅጣት መለያየት የፍትህ ሥርዓቱን ተገማች እንዳይሆን ያደርጋል ዜጐች በፍትህ ሥርዓቱ ያላቸው እምነት እንዲሸረሸር ያደርጋል በሚል ምክንያት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በመሆኑም ዐ/ህግ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መከራከሪያ ነጥብም ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተነናል፡፡ ዐ/ሕግ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ከላይ በዝርዝር በተመለከትናቸው ህጋዊያን ምክንያቶች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተትን ሊያሟላ የሚችል ባለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሠሚው ችሎት በተጠሪው ላይ ያስተላለፈው የ2/ሁለት/ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ውሣኔ የሚጨመርበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

የተጠሪ ጠበቆች ይግባኝ ሠሚው ችሎት ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ ተጠሪ በጠቅላላው ክፍል ለጽኑ እሥራትና ለቀላል እስራት መነሻ የሆኑትን ጊዜያት መቀጣት ሲገባቸው በ2/ሁለት/ ዓመት ጽኑ እስራት እነዲቀጡ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑን ጠቅሰው ይህ ችሎት በህጉ የተሰጠውን ስልጣን ተጠቅሞ ተጠሪ የታሰሩትን በቂ አድርጐ ከእስር እንዲለቀቁ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ የወንጀል ጉዳይ ይግባኝ የሚመራበትን

ሥርዓት የሚደነግገው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2)(መ) በቅጣቱ ላይ ብቻ ይግባኝ በተባለ ጊዜ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ቅጣቱን ያፀናል ይጨምራል ወይም ይቀንሣል ሲል ይደነገጋል፡፡ የዚህን ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና መንፈስ ስንመለከተው የቅጣት ማጽናት መጨመር ወይም መቀነስ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓት የሚከናወነው ይግባኝ አቅራቢውን ጥያቄ ከህጉ ጋር በማገናዘብ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሥርዓቱን ጠብቆ አቤቱታ ላላቀረበ ወገን ሌላው ተከራካሪ ወገን አቤቱታ ባቀረበበት መዝገብ ቅጣት የሚቀነስበት ሥርዓት ስለመኖሩ ሥነ ሥረዓቱ አያሣይም፡፡ የተጠሪ ጠበቆች የዳኝነት ጥያቄ ከይግባኝ ሥርዓት አቀራረብና መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን ጥያቄ ለመቀበል የሚያስችለን ሥነ ሥርዓት የለም በማለት አልፈነዋል፡፡

በመጨረሻም ዐ/ህግ የገንዘብ መቀጫውን በተመለከተ ያቀረቡት ቅሬታ ተመልክተናል፡፡ የስር ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ ያስተላለፈው የገንዘብ መቀጮ በድምሩ ብር 18,000.00 /አሥራ ስምንት ሺህ/ ነው፡፡ ይግባኝ ሠሚው ችሎት በበኩሉ ተጠሪ በብር 11,000.00 /አሥራ አንድ ሺህ/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ በመግለጽ የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሠጠውን ውሣኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ ይግባኝ ሠሚው ችሎት ለቅጣት ውሣኔው መሻሻል መሠረት ያደረገው ምክንያት ምን እንደሆነ በውሣኔው ላይ አላመለከተም፡፡ ለእስራት ቅጣቱ መቀነስ ዋቢ የተደረገው የወንጀል ህግ አንቀጽ 179(ሐ) ሲሆን ይህ ድንጋጌ ለገንዘብ መቀጮም መሠረት የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይኸው ድንጋጌ በግልጽ የሚያሣየው የእስራት ቅጣት አወሣሰን በተመለከተ ነውና፡፡

በመሠረቱ የገንዘብ መቀጮ የሚደረገው ቅጣት የሚወሰነው ዘወትር ከተቀጭው አቅም ጋር የተመዛዘነ ሊሆን የሚችልበት ዘዴ በመፈለግ የተቀጭውን የዕድሜና ጤንነቱን ሁኔታና የሀብቱን

ምንጭ ስለቤተሠቦቹ አስተዳደር ያለበትን ሸክም፣ የሞያ ስራውንና በዚህም ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም በመገመትና ቅጣቱም ከፈፀመው ጥፋት ጋር ተመዛዛኝ ሆኖ ስለመሆኑ ህጉ በአንቀጽ 90(2) ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የአከፋፈሉ ሁኔታም የተቀጭውን መብት በጠበቀ መልኩ መሆን እንደሚገባው በህጉ ከአንቀጽ 90 እስከ 97 ድረስ የሠፈሩት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የገንዘብ መቀጮ መጠን አቀናነስ በምክንያት አለመደገፉ በገንዘብ መቀጮ የሚደረገው ቅጣት አወሣሰን መርሆዎችን በተመለከተ ህጉ ያስቀመጠውን አካሄድና ዓላማ ያላገናዘበ መሠረታዊ የሆኑ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆኑም በዚህ ረገድ የይግባኝ ሠሚው ችሎት የሠጠው ውሣኔ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 62266 ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሠሚ ችሎት በመ/ቁ 41954 የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የተሻሻለውን ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(መ) መሠረት፡-

   ሀ/ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው ለሁለቱም ጥፋቶች 2(ሁለት) ዓመት ጽኑ እስራት ነው በማለት ይግባኝ ሠሚው ችሎት የሠጠውን ውሣኔ አጽንተናል፡፡ የእስራት ቅጣቱ የሚታሰበውም ተጠሪ በጉዳዩ ላይ እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ነው ብለናል፡፡

   ለ/ የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ግን ይግባኝ ሠሚው ችሎት የሠጠውን ውሣኔ ባለመቀበል የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሠጠውን የውሳኔ ክፍል

አጽንተን ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በብር 18,000.00 /አስራ ስምንት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ነው ብለናል፡፡

2. ውሳኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማረ/ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡ ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ ለፍ/ቤቶቹ ግልባጭ ይተላለፍላቸው ብለናል፡፡

3. የፌ/ከ/ፍ/ቤት መ/ቁ 62266 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ ብለናል መዝገቡ ያለቀለት በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ